     

1923 2002

# ትውስታ ለሙዚቃው ቀማሪ

የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ በእሁዱ ዕለት ዜናው፣ የእውቁን የሙዚቃ ደራሲና ቀማሪ፣ የኮ/ል ሣህሌ ደጋጎን ዜና እረፍት ሲያሰማን፣ አዘንኩኝ:: በትዝታ ወደኋላ በመመለስም የልጅነት ጊዜዬን ማሰላሰል ያዝኩኝ:: የሙዚቃ በረከት እየመገቡ ላሳደጉን ለኒያ ታላቅ የሙዚቃ ሰው ያለኝን ከበሬታ ለመግለጽም ይህቺን አጭር ማስታወሻ ለማስተላለፍ ወደደኩ::

ያደግሁት አዲስ አበባ ከጃንሜዳ - እስከ ፈረንሳይ ለጋሲዮን ባለው ሰፈር በመሆኑ፣የክብር ዘበኛ ሙዚቃ ባንድ፣ በየክብረ በዓላቱ በተለይም ስድስት ኪሎና አራት ኪሎ የሚገኙትን መታሰቢያ ሐውልቶች እየዞረ፣ ጣዕም ያላቸውን የማርሽ ሙዚቃዎች ሲያሰማ፣ ልጆች ሆነን ከኋላ-ኋላ እየተከተልን ነፍሳችንን እናስደስት ነበር::

በተጨማሪም በየዓመቱ ለክብር ዘበኛ ቤተሰቦች በሚዘጋጅ የሙዚቃ ትርዒት(ኮንሰርት)፣ ከጃንሜዳ ፊት-ለፊት በሚገኘው የክብር ዘበኛ የሙዚቃ ክፍል ቅጽር ጊቢ ውስጥ፣ ሜዳ ላይ መድረክ ተዘጋጅቶ፣ እነ ጥላሁን ገሠሠ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ እነ ተፈራ ካሳ፣ እነ ተዘራ ኃይለ ሚካኤል.. እና ሌሎችም እውቅ ድምጻዊያን፣ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾችና ተወዛዋዦች የሙዚቃን ጥበብ በነጻ ያስኮሞኩሙን ነበር::

ታዲያ! የዚያ ሁሉ ጥበብ የጀርባ አጥንት በመሆን፣ ያንን በሕይወት ዘመን ሁሉ የማይረሳ የሙዚቃ ቃና ከሚቀምሩት መሃል ዋነኛው ሣህሌ ደጋጎ ነበሩ:: በተለይ የሣህሌ ደጋጎን የሙዚቃ ቅመራ በእጅጉ ማድነቅ የጀመርኩት፣ በያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት የሙዚቃን ሳይንስ ትምህርት ከቀሰምኩ በኋላ ነበር::
የጥላሁንን፣ የብዙነሽን፣ የመሐሙድን እና የሌሎችንም ድምጻውያን ነባር ዜማዎች ሳዳምጥ፣ ከድምጻውያኑ በስተጀርባ ከውስጥ ዘልቄ እያንዳንዱ የሙዚቃ መሳሪያ የሚያደርገውን «ምርጥ ሙዚቃዊ ንግግር» ማዳመጡ፣ የሚሰጠኝ መንፈሳዊ እርካታና፣ የቀማሪው የላቀ ሙያዊ ብቃት የሚፈጥርብኝ ግርምታ ሁሌም ከኔው ጋር ናቸው::

ሣህሌ ደጋጎና አብዛኛዎቹ የክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ባልደረቦች ነዋሪነታቸው እኔ ያደግሁበት አካባቢ የነበረ በመሆኑ፣ ዘወትር ወደ ስራቸው በእግራቸው ሲመላለሱ የማየት እድል ይገጥመኝ ነበር:: እናም ሣህሌ ደጋጎ፣ ሁሌም ከእጃቸው የማትለየውን ደብተር አንግበው መሬት መሬት እያዩ ሲያዘግሙ፣ ሥዕሉ እስከዛሬም ድረስ ውስጤ ተቀርጾ ይታየኛል::

የዚያችን ደብተር ምስጢር ያወቅሁት ደግሞ፣ ባንድ ወቅት ከኢትዮጵያ ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ይመስለኛል:: እንዲህ ነው፤ ባንድ ዕለት ወደ ስራቸው ሲያዘግሙ፣ የዜማ ይሁን የግጥም ፈጠራ መንገድ ላይ ድንገት መጥቶላቸው ያስጨንቃቸዋል:: ከዘገየ እንዳይጠፋባቸው፣ በመስጋት ወዲያውኑ
«እዚያች ደብተር» ላይ ሊከትቡ ማስደገፊያ ሲፈልጉ፣ ሳያስቡት መንገድ ዳር ወደሚገኝ ቤት ግድግዳ ጠጋ ብለው መጫጫሩን ይያያዙታል:: በዚህን ጊዜ የቤቱ ባለቤት በሩን ከፍታ ትወጣና «የመብራት ነው? የውሃ ቆጣሪ?» ትላቸዋለች. . .::

ኮ/ል ሣህሌ ደጋጎ፣ «የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ወርቃማው ዘመን» እየተባለ በሚታወቀውና፣ ዘመናዊ ሙዚቃ በአገራችን ባበበባቸው የሺ ዘጠኝ መቶ ሃምሳና ስድሳዎቹ ዓመታት ውስጥ ነጥረው የወጡ ኮከብ ሙዚቀኛ ነበሩ:: ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ዕድገት ላደረጉት የላቀ አስተዋጽዖና ለዋሉልን ታላቅ ውለታ፣ ትውልድ ሲያስታውሳቸው ይኖራል::

ለቤተሰብ፣ ለወዳጅ ዘመድና ለሙዚቃ አፍቃሪያን በሙሉ መጽናናት ይሁን!

ጌታቸው አበራ
መጋቢት ፯ ቀን ፪ ሺ ፪ ዓ/ም
( ማርች 2010)